# ክፍል ሦስት / ፈቃድና ሃላፊነት

<u>ለክፍል ሁለት ት/ት ማሰሪያ</u>
ጥንቃቄ ይጠብቅሃል... (ምሳ 2:11) ቢልም ...እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፥ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል። (መዝ 127:1)

እርሱ የወደደውን ሁሉ ያደርጋል:: የሚሆነው ሁሉ ግን እርሱ እንዲሆን ይፍቀደው እንጂ የግድ (necessarily) እርሱ የወደደው ነው ማለት አይደለም:: (ለምሳሌ:- የእስራኤል በንጉሥ መመራት...)

የእ/ር መፍቀድ በሁሉም ነገር <u>ምክንያታዊ ተደርጎ መታየት የለበትም!</u>

የእ/ር ሉዓላዊ ፈቃድ ሊቀለበስ አይችልም! [መዝ 135:6 በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች ሁሉ፥ እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ አደረገ። / He does whatever he pleases... ኢዮብ 42:2 ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።]

የይሁን ፈቃዱም ተቀናብሮ ፍጹም ፈቃዱን ያገለግላል! (ለምሳሌ:- የዮሴፍ ለባርነት መሸጥ)

<u>ሰው የእ/ር ስህተት(defect) አይደለም! ሰው የምርጫውም ውጤት ነው!</u>
አዳም በተፈጠረ ጊዜ እ/ርን የሚመስልና በመንፈስም በአካልም <u>የበሰለ/ ሙሉ ሰው</u> ነበረ:: ስለዚህም በእ/ር ፍጹም ፈቃድ መኖር ይጠበቅበት ነበር:: ለሕይወት የሚያስፈልገው ነገር ሁሉም ተሰጥቶት ነበረ፤ ሕይወትና ሞትም በፊቱ ነበሩ:: (ዘፍ 2:9) የእ/ር ፍላጎት/የልቡ ደስታ/ ፍጹም ፈቃዱ አዳም ሕይወትን መርጦ ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንዲኖር ነበር::

↓

የመጀመሪያው አዳም ግን ከሕይወት ይልቅ እ/ርን ባለመታዘዝ የሞትን መንገድ መረጠ፤ ከእ/ርም ተለየ:: [ዘፍ 3:1- ]

↓

ከውድቀት በኋላም ሰው ልቡ ከእ/ር እየራቀና እልከኛ እየሆነ ሄደ:: *[ዘፍ 4:6-8፣ 6:5፣ 11:1-9 / ከቃየን ገዳይነት ጀምሮ የውሃ ጥፋት ከዛም የባቢሎን ግንብ - በተለይ ዘፍ 6:5 እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ <u>የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ</u> አየ። ይለናል]* እስከ ሙሴ ድረስም ሞት ነገሰ:: *[ሮሜ 5:14 ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ <u>ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤</u> አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና።]*

↓

ይሁን እንጂ እ/ር ሰውን ፈጽሞ ሊያጠፋው ስላልወደደ በድካሙ ሊቀበለው በሙሴ ሕግን ሰጠው:: *[ዘፀ 20:ሙሉውን; ማቴ 19:8 እርሱም፦ <u>ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ</u> ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።]*

↓

ሆኖም ሰው ለእልከኝነቱ በተመቸው የሙሴ ሕግ ወደ ፍጹምነት ሊደርስ አልቻለም:: [*ሮሜ 9:31-32 እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ <u>ወደ ሕግ አልደረሱም</u>። ይህስ ስለ ምንድር ነው? በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው፤ ገላ 3:24 እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤]*

↓

ቀድሞም/የዘላለም ሃሳቡ ሰው በእርሱ መልክ ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንዲኖር የነበረ እ/ር በአዲስ ኪዳን ለሰው ወደ ቀደመው ስፍራ የመመለስ ሁለተኛ እድል ሰጠው:: ሁለተኛው አዳም ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሁሉ እንደ እኛ ተፈትኖ ያለ እንከን በመኖርና እስከሞትም በመታዘዝ በወሰደው ምርጫ ዳግም ሕያዋን ሆንን። [*1ኛ ቆሮ 15:22 ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።... እንዲሁ ደግሞ። ሮሜ 5:17-19 በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል <u>በሕይወት ይነግሣሉ</u>። እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት*

*ፍርድ ለኩነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።]*

↓

ከምንጊዜውም ይልቅ በፍጹም ፈቃዱ የመኖር ብቃት ያለውን አዲስ ሕይወትን/ማንነትን ሰጥቶን እንደመጀመሪያው ሁሉ በእርሱ መልክ እንደ እርሱ ፍጹማን ሁነን እንድንኖር ጠየቀን:: [*ኤፌ 4:22-24 ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥ ለእውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።]*

## የፈቃድን / የምርጫና ውሳኔን አቅጣጫ የሚወስኑ ነገሮች

ኤፌ 2:1-3 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።

1) *የሥጋ ምኞት/ ስሜት*
   *ቦና /እውቀት /መረዳት* / intellect / understanding

2ኛ ጴጥ 2:19 ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና።

ሮሜ 8:5፣ 12-13 እንደ *ሥጋ ፈቃድ* የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። ...እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ *ለሥጋ አይደለም*። እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ።

## ፈቃዳችን/ ምርጫዎቻችንና ውሳኔዎቻችን ሃላፊነቶቻችን ናቸው

ነጻነት ከሌለ ምርጫ የለም፤ ምርጫ ከሌለ ሃላፊነት የለም፤ ሃላፊነት ከሌለ ተጠያቂነት/ፍርድ የለም፤ ፍርድ ከሌለ ደግሞ ፈራጅ/ ዳኛ የለም/ አያስፈልግም!

- ነጻ አውጭ ከሌለ ደግሞ ነጻነት የለም! ነጻ አውጭው ዳኛውም እርሱ ነው! *[ዮሐ 8:32፣36 እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።... እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ። ገላ 5:1 በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።]*
- እነዚህ ሁሉ ነገሮች ስለመኖራቸው ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የተቀመጠ ጉዳይ ነው።
- እነዚህ ነገሮች እንደሰንሰለት የተያያዙና አንዱን ከመሃል ብናነድል ወይንም እንደሌለ ብናስብ የምንስትበት ጉዳይ ነው።

## ሃላፊነትን መሸሽ / escapism

ለወሰዱት ምርጫ ሃላፊነትን ያለመውሰድ ችግር በአዳም የተጀመረ... ዛሬም ግን የቀጠለ ጉዳይ ነው:: በአንጻሩ እንደ ዳዊት ያሉ ትሁታን ለምርጫቸው ሃላፊነትን ሲወስዱ የእ/ርንም ሞገስ ሲያገኙ አይተናል::

በሰው ሁሉ ልብ ውስጥ ስለነገ (future) ማሰብና ነገውን የመወሰን/ የመምረጥ ፍላጎት አለ:: ሰው ከተፈጠረበት ማንነት የተነሳ ነጻ ምርጫውን መለማመድ ይፈልጋል። ሆኖም ግን ሰዎች በዘመናቸው ሁሉ የምርጫቸውን ውጤት ለመቀበልና ሃላፊነቱን ለመውሰድ ስለማይፈልጉ ብዙ ማምለጫዎች ሲያበጁ ኖረናል። ለዚህ ምሳሌዎች ከሚሆኑት:

**1) እ/ር የለሽ ዘገምተኛ ለውጥ (atheistic evolution) አስተምህሮ**
ይህ አስተምህሮ ዓለምና በውስጧ ያሉት ነገሮች ሁሳ በጊዜና በእድል ቀስ በቀስ የተወሰኑና እየተወሰኑ የሚሄዱ ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ በማቅረብ የዓለማትን ባለቤት ከሥፍራው ለማስወጣት ይሞክራል:: ባለቤት (ዳኛ) ከሌለ ደግሞ ተጠያቂነት የለም! ስለዚህም ሰዎች ለሃጢያት ምርጫዎቻቸው ሃላፊነት ሊሰማቸው እንደማያስፈልግ አድርጎ በሾላካ (subtle) መንገድ የሰዎችን አእምሮ ይጠመዝዛል።

> በቤ/ክንም ነገር ሁሉ በፊቱ የተራቆተና የተገለጠ እ/ር እንደማያይ ሲመስል ሰዎች እንደፈለጉ ሲወጡ ሲገቡ፣ ወይንም ቤቱን አደራ ሰጥቶን የሄደው ጌታ የማይመለስ ሲመስለንና ፍርድን ስናዛባ የዛን ጊዜ ወዮልን!

**2) የመወሰን (determinism) ሥነ-ልቦና አስተምህሮ**
የዚህ አስተምህሮ መሠረታዊ ሃሳብ የአንድ ሰው (በሽተኛ) ባህሪይ የሚወሰነው ከእርሱ ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ለምሳሌ እንደ ቤተሰብ፣ ሃይማኖት ባሉ ነገሮች ስለሆነ ለሚወስዳቸው መጥፎ እርምጃዎች ውጫዊ ምክንያቶችን ዋና ተጠያቂ ያደርጋል። በዚህም ተጠያቂነትን በማስወገድ ለአመጽ መስፋፋት መንገድ ይከፍታል።

> ዛሬ ብዙ ወንጀለኞች በዚህ መንገድ "ነጻ" ሆነዋል!
> በሽታንና የባህሪይ ችግሮቻችንን ከቤተሰብ የተወረሰ አድርገን የምናስብ ከሆነ በምን ተሻልን?

**3) የከዋክብት ቆጠራ (astrology)**
የሰው ዕጣ (fate) በከዋክብት ውስጥ እንደተቀመጠ አድርጎ በማቅረብ ሰዎች ፍጻሜያቸው (destiny) ያለአግባብ እንዲወሰንና በሕይወታቸው ለሚሆነው ነገር ግብረገባዊ ሃላፊነት እንዳይወስዱ ያደርጋል።

> ከተጻፈው የእ/ር ቃል ይልቅ ባልተመረመሩ ትንቢቶች ሕይወታቸውን የሚመሠርቱ ክርስቲያኖች በምን ተሻሉ?

**4) የሃይማኖት አስተምህሮዎች**
ከሁሉም ይልቅ የተሳሳቱ የሃይማኖት አስተምህሮዎች ወይንም አመለካከቶች ሰው ሃላፊነቱን የሚሸሽባቸው ብዙ መንገዶችን ፈጥረዋል። በሌሎች ሃይማኖቶች ያለውን ትተን በቤ/ክ እንኳን በምድር ያለውን መከራና ችግር እ/ር ስለፈቀደ  እንደሆነ  ወይንም በጭፍን ለሌሎች ሰዎች ሃጢያት የተሰጠ የእ/ር ፍርድ እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ ስለዚህም ምንም ማድረግ እንደማንችል፣ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚያልፉ ሰዎችን በሰማይ ስላለው ተስፋ እያሰቡ እንዲጽናኑ እንጂ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ አይነት ...ወዘተ የሚመክሩ ብዙ አስተምህሮቶች አሉ።

> እንዲህ ካለ (የኢዮብ ወዳጆች) አጽናኝነት ይጠብቀን!
> ስለመነጠቅ ወይንም ስለጌታ መምጣት ያለን የተዛባ መረዳት በምድር የተሰጠንን ሃላፊነት ላለመወጣት ምክንያት (excuse) የሆነበት ሁኔታ ብዙ ነው።
> ዘላለማዊነትን ብቻ እያወራን የሥጋ ሞት እንዳለ የሰውም ሕይወት አጭር እንደሆነ ብንዘነጋ ምንኛ ምስኪኖች ነን!
> የጌታ መምጣትም ሆነ የሥጋ ሞት የምድር ዘመናችን ለሥራ የተሰጠን ቀን ውሱን መሆኑንና ቀን ሳለ የተሰጠንን ሥራ እንድንሰራ/ ሃላፊነታችንን እንድንወጣ የሚያሳስቡን ነገሮች ናቸው።

**5) መጠጥ አደንዛዥ እጽና ሱሶች**
…

ሰው በውስጡ ሃላፊነትን በመሸሽ ነጻ መሆን የሚችል ይመስለዋል፤ እውነታው ግን ሃላፊነትን መሸሽ ሰውን ልቅ እንጂ ነጻ አያደርገውም። … *[ገላ 5:13 ወንድሞች ሆይ÷ እናንተ ለአርነት*

*ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።]*
ይልቁን እውነተኛ ነጻነት የሃላፊነት መንገድ ነው። *[1ኛ ቆሮ 6:12 ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም። 1ኛ ቆሮ 10:23 ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም።]*

ያመኑም ያላመኑም ሁላችንም  ለምርጫዎቻችንና ለሥራችን ተጠያቂነት አለብን *[2ኛ ቆሮ 5:10 መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።]*

**ሃላፊነትን የመሸሽ ውጤቶች**
መሪ አልባ መሬት! የሚያምነውም የማያምነውም ሁሉም ከሸሸ...

የክፋት በምድር መባባስ…

“ሰው አጣሁ” የሚለው የእ/ር ድምጽ በየዘመኑ ሲሰማ የኖረና ዛሬም በተለያየ መልክ የሚሰማ ነው!